# "ብርሃኑም፣ ልደቱም የለም"

ውድነህ ተስፋዬ
ዊኒፔግ፤ ካናዳ

እንዴት ሰነበታችሁሳ! ገና እንዴት ነበር? የፈረንጆቹን ገና ላከበራችሁ ማለቴ ነው መቼም ልጆቻቸውን በውጭ የወለዱ የግዴታ ለልጆቻቸው ሲሉ የፈረንጁንም የኢትዮጵያውያንም ገና እንደሚያከብሩ ነው። "የገና አባትን" (Santa Clause) እንደ ልጆች አሻንኩሊት ወይም መጫወቻ ይገዛልኝ እንደሚሉት እኔም፤ ወገኑ በጎሰኛው ወያኔ ሥርዓት ሲታሰር፣ ሲገደል መፈጠሩን እስኪጠላ ሲሰቃይ ወላፈኑ እኔን አልነካኝም በሚል በሥርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑ፣ በንዋይ ሰክረው በግል ጥቅም የታወሩትን ግብዞች የሚያስተውል ልብና አህምሮ እንዲሰጣቸው በጠየኩ ነበር።

የገና በዓል ለወጣቱ መቼም ከስጦታ መለዋወጥና በየቦታው በጭፈራ ከማሳለፍ የበለጠ የሚያስደስተው አይኖርም። ሌላው የገና በዓልን ከስጦታ መለዋወጥ አልፎ ፊቱን አጨፍግጎ በስራ የተወጠረው ነዋሪ ሁሉ "*ሜሪ ክሪስ ማስ*" እያለ ሞቅ ባለ ፈገግታ ሰላምታ ሲሰጥ ማስተዋሉም አንድ የገና በዓል መንፈስ ነው። በአሁኑ ዘመን በተለይም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ደግሞ መረን በለቀቀ መልኩ ገና ከሀይማኖት በዓላት ወጥቶ የሸቀጥ ማስታወቂያ ሲሆን መታየቱ ነው።

እንግዲህ የውጩን ገና በዚህ እንቋጨውና ከወደ አገር ቤት የመጣ አንድ ቀልድ ፈገግ አድርጎኝ ነበር፣ ሆኖም ቀልዱን ከቀልድነቱ አልፎ የኢትዮጵያ ሕዝብ በውጭ ካለው ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ አስተሳሰቡ ምን ያህል ቀድሞ እንደሄደ ነው። ለዚህ ፅሁፍም አርዕስት ያሰጠኝ ይሄው ቀልድ ነበር፣ ከአሜሪካ ወደ አገር ቤት ዘመዶቹ ጋር ስልክ ደውሎ፣ እሱ ባሳለፈው የፈረንጆቹ ገና እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ ሲል የተሰጠው መልስ " ብርሃኑም፣ ልደቱም የሉም " ምንድ ነው የምትለው ብለው ያሳቁትን ነው።

አዎ የኢትዮጵያ ሕዝብማ ማን ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። ነፃ ሚዲያ በታፈነበት ሁኔታ እዚህ ያለውን የፖለቲካ ትኩሳት በየሰኮንዱ የምትደረገውን በተጨባጭ መረጃ ይከታተላል። ብርሃኑ ማን እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ያው ወደ ወያኔ ጎራ ከትቶት ከልደቱ ጋር ቀይጦት "ብርሃኑም ልደቱም" የሉም በቁም የፖለቲካ ሞታቸውን ሞተዋል ብለው ባገኙት አጋጣሚ ብሶታቸውን መግለጻቸው ነበር። መቼም ከዚህ የዳያስፖራው ፖለቲከኛ ልብ ገዝቶ መማር ያለበት ይመስለኛል። እዚህ በዲያስፖራው አንድ ሰሞንማ ብርሃኑ ጻፈው የተባለውን መጽሐፍ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚያ ጥቅስ ሊጠቅሱልን የሚቃጣቸው አቶ አንዳርጋቸው

የመለመላቸው ካድሬዎችም ነበሩ፤ የዛሬን አያድርገውና እንዲህ ጉዳቸው ሊወጣ ሲያልቅ አያምር አሉ አሁንማ አይደለም መጽሐፉን ሊያዳምጣቸው ቀርቶ ራሱ ብርሃኑ ስለ ፖለቲካ ባያወራ ይመርጣል ምክንያቱም ምንም እውነት ሊናገር አልቻለም። ጧት የተናገረውን ማታ የማይደግመው ሆነ።

የብርሃኑ የፖለቲካ ትግል እዚያው የሱ ውዳሴ ከሚሰማበት ከከረንት አፌይርስ ፓል ቶክ ክፍል አያልፍም የኢትዮጵያ ህዝብማ እንኳን በብርሃኑ የሚመራ ቅንጅት ነኝ ብሎ የሚመጣን ድርጅትን ሊቀበል ቀርቶ መሰብሰቢያ አዳራሽም ነፍጓቸዋል። ማን የሕዝብ መሪ እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃልና ስለዚህ ለነብርሃኑ የሕዝብ መሰረት ለሌለው የጨጨታ ፖለቲካቸው ጊዜና ቦታ የለውም። ያው በሪሞት ኮንትሮል ትግሉን እመራለሁ ብሎ ስለሱ አጋነው በሚያራግቡለት በጅምላ በያዛቸው ሚዲያ የሚደነቁር ካገኙ ይሞክሩ እንጂ እኛስ ነቄ ብለናል።

ይኸውላችሁ ታላቁና ታሪካዊው የግንቦት 97ቱ ምርጫ መዝገብ ገና አልተዘጋም። ወያኔ የተቻለውን ያህል ሊያፍነው ቢጥርም በበረከት ስምኦን ትእዛዝ በብርሃኑ ወኪልነት አማካኝነት ቅንጅትን አፍርሶ ስለሚቀጥለው ምርጫ ዝግጅት ሽር ጉድ ማለቱን ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ሕዝብ ግን የተሰረቀው ድምጼ ይከበር እያለ ባገኘው አጋጣሚ እየገለፀ ነው። ባለፈው ወርም በታላቁ ሩጫ ላይም ታይቷል፤ ታላቁ ሩጫ፣ ብሶት መግለጫ! ፤ ደም፣ደም ይሸታል ቤቱ፣ ቤተ መንግስቱ! በአርባ ብራችን ነፃነታችን! የሚሉትን ሌሎችም መፈክሮች በድፍረት እያሰማ ብሶቱን ገልፆ ነበር። ስለዚህ እዚህ ያለው ድጋፍ ሰጪ ድርጅት እንጂ የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም። በጣም የሚገርመው በብርሃኑ አዛዥነትና በአንዳርጋቸው የተሰየሙት ተለጣፊ ድርጅቶች እራሳቸውን የፖለቲካ አባል አድርገው ሾመው በየከተማው ተሰይመው የስልጣን ተስፈኞች ሆነዋል ምስኪኖች። አቦ ከአገር ቤቶቹ ተማሩ፣ትግሉ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው በውጭ ያለው በዲፕሎማሲና በገንዘብ ትግሉን መርዳት እንጂ ከዚያ አልፎ ትግሉ ከአገር ቤት አይወጣም።

የእኛ ገና እስኪመጣ ድረስ “እንኳን ለብርሃነ ልደቱ” በሰላም አደረሳችሁ!! አዬ የኔ ነገር፣ ይቅርታ ለካ ብርሃኑም ልደቱም የለም ነው መልሱ። እንኳን ለገና በዓል አደረሳችሁ!! መልካም ገና ይሁንላችሁ፤ በቸር ይግጠመን!!

የሕዝብ ድምፅ ይከበር!!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

ታህሳስ 17 ቀን 2000